# ራዳር የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ

## የትራፊክ መብራት

### 1. የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራት

በመገናኛ ሥፍራዎች ከተለያየ አቅጣጫ በመምጣት ላይ የሚገኙ አሽከርካሪዎችና እግረኞች ሥርዓትን በያዘ መንገድ በየተራ መተላለፍ እንዲችሉ በተለያዩ ቀለማት ባላቸው መብራቶች መልዕክት የሚያስተላልፉ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡

የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች በሚሰጡት አገልግሎት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፦

1ኛ- ***የእግረኞች ማስተላለፊያ መብራት፡-*** እግረኞችም ሆኑ ተሽከርካሪዎች በሚንቀሳቀሱበት ወቅት መንገድ እንዳያቋርጡ እንዲሁም ተሽከርካሪዎች በሚቆሙበት ጊዜ መንገድ ማቋረጥ እንዲችሉ የተለያየ ቀለም ባላቸው መብራቶች መልዕክት የሚያስተላልፍ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ ሲሆን በውስጡም ከተሽከርካሪ መተላለፊያ መብራት መለየት እንዲቻል የእግረኞች ሥዕል ይኖራቸዋል፡፡



ሀ/ ቀይ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት ሲበራ እግረኞች መንገድ እንዲያቋርጡ አይፍቀድላቸውም፣

ለ/ አረንጓዴ የእግረኛ ምስል ያለበት ሲበራ እግረኞች ለመተላለፊያ በተሰመረ መስመር ውስጥ ብቻ እንዲያቋርጡ ይፈቀድላቸዋል፡፡





## 2- *የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት*

ከተለያየ አቅጣጫ ወደ መገናኛው መንገድ በመምጣት ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች በየተራ እንዲተላለፉ የሚያደርግ መብራት ሲሆን ከእግረኞች ማስተላለፊያ ጋር በቅንጅት ተሽከርካሪና እግረኞች በየተራ እንዲተላለፉ በማድረግ አደጋ እንዳይፈጠርና የትራፊክ መጨናነቅን ለመቀነስ የሚረዱ የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ከላይ ወደታች ቀይ፣ቢጫና አረንጓዴ ቀለም ሲኖራቸው በአበራር የሚከተለውን ትርጉም ይሰጣሉ፡፡

### 2.1. *ቀይ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ፦*



በሚበራበት አቅጣጫ ያሉ ተሽከርካሪዎች ለእግረኛ መተላለፊያ የተሰመረውን መስመር ሳያልፍ መቆም አለባቸው፡፡ ቀይ መብራት እየበራ አልፎ መሄድ በህግ ከማስጠየቁም በተጨማሪ ለአደጋ ያጋልጣል፡፡



**2.2. *ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ፦*** ማንኛውም አሽከርካሪ በመንገዱ ላይ አደገኛ ሁኔታ እንዳለ ተገንዝቦ ለእግረኛ መተላለፊያ የተሰመረውን መስመር ሳያልፍ በመቆም አደጋ የማያስከትል መሆኑን ሳያረጋግጥ እንዲያልፍ አይፈቀድለትም፡፡ ይህ መብራት በባቡር ሐዲድ ማቋረጫ፣ ባቡር በሚያልፍ ጊዜና በመገናኛ ሥፍራዎች ላይ የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ሲንቀሳቀሱ ወይም ሌላ አደገኛ ሁኔታ ሲኖር የሚበራ ሲሆን የተላለፈውን መልዕክት በመተላለፍ መንገድ ለማቋረጥ መሞከር ለአሰቃቂ አደጋ ከማጋለጡ በተጨማሪ በሕግ ያስቀጣል፡፡

### 2.3. *ቀይና ቢጫ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራቶች በአንድነት ሲበሩ፣*

- ⇨ በቀይ መብራት ቆመው የነበሩ አሽከርካሪዎች ለመሄድ ይዘጋጃሉ፣

⇨ ወደ መገናኛው መንገድ በመድረስ ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች ከእግረኛ መተላለፊያ መስመር ሳያልፉ በመቆም ለመሄድ ይዘጋጃሉ፡፡

2.4. ***አረንጓዴ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ፦*** ይህ አሽከርካሪዎች ቀድመው ወደ መረጡት አቅጣጫ ማለፍ አለባቸው በዚህም ወቅት ዘግይተው በእግረኛ መተላለፊያ ውስጥ በማለፍ ላይ ላሉ እግረኞች ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡



2.5. *ቢጫ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ብቻውን ሲበራ*

ይህ መብራት ከአረንጓዴ መብራት ቀጥሎ ሲበራ፦

⇨ ወደ መገናኛው መንገድ በመምጣት ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች ለእግረኛ መተላለፊያ የተሰመረውን መስመር ሳያልፉ ይቆማሉ፣

⇨ ወደ መገናኛው መንገድ ቀድመው የገቡ አሽከርካሪዎች በፍጥነት መንገዱን ለቀው መውጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡





2.6. ***ብልጭ ድርግም የሚል ቢጫ የተሽከርካሪ ማስተላለፊያ መብራት ሲበራ፤*** አሽከርካሪው በመንገዱ ላይ አደገኛ ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ፍጥነቱን በመቀነስ ለተላላፊዎች ቅድሚያ በመስጠት በጥንቃቄ ማለፍ ይችላል፡፡ ይህ መብራት በአብዛኛው የትራፊክ መጨናነቅ በማይበዛበት ወቅት ለምሳሌ በምሽት አሽከርካሪዎች ሌሎች ተላላፊዎች ሳይኖሩ ለረጅም ሰዓት እንዳይቆሙ እንደሁኔታው በጥንቃቄ መተላለፍ እንዲችሉ ሊያገለግል ይችላል፡፡

2.7. ***መብራቶች ጎን ለጎን በጥንድ ሆነው ከተዘጋጁ የሚያስተላልፉት መልዕክትም ጥንድ ይሆናል፡፡***

1. ሀ. ቀይ መብራት በበራበት በኩል ቀስቱ እንደሚያመለክተው ወደ ግራ የሚታጠፉት አሽከርካሪዎች ይቆማሉ፡፡

ለ. አረንጓዴ መብራት በበራበት በኩል ቀስቱ እንደሚያመለክተው ቀጥታ ፊት ለፊትና ወደ ቀኝ ለሚሔዱ አሽከርካሪዎች ጉዞ እንዲቀጥሉ ስለተፈቀደላቸው መሔድ አለባቸው፡፡



1. ሀ. አረንጓዴ በበራበት በኩል ቀስቱ እንደሚያመለክተው ወደ ግራ ለሚታጠፉት አሽከርካሪዎች እንዲጓዙ ተፈቅዶላቸዋል።

ለ. በቀዩ መብራት በኩል ከአናቱ ፊት ለፊት ወይም ወደ ቀኝ ታጥፈው የሚጓዙ አሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ይገደዳሉ።



## 1.3 የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክቶች

ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከፊት ለፊት የሚመጡትን አሽከርካሪዎች ያስቆማል። በመሆኑም የትራፊክ ፖሊሱ ለማስቆም ይህን የእጅ ምልክት ሲያሳይ አሽከርካሪዎች እግረኛ ማቋረጫ መስመር ውስጥ ሳይገቡና የማቆሚያ መስመሩን ሳያልፉ ትክክለኛ ረድፋቸውን ይዞ የመቆም ግዴታ አለባቸው።





ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከኋላ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን ያስቆማል።

ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከፊት ለፊትና ከኋላ ወደ መስቀለ መንገድ የሚመጡትን ተሽከርካሪ ዎች ያስቆማል።





ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ፊት ለፊት ቆመው የነበሩ አሽከርካሪ ዎች ወደ ፊትና ወደ ቀኝ እንዲጓዙ ይፈቅዳል።

የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከቀኝ ወደ ግራ ቀጥታ፣ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ታጥፈው የሚሄዱ አሽከርካሪዎች እንዲያልፉ ይፈቅ ዳል።





ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከኋላ ቆመው የነበሩ አሽከርካሪዎች ቀጥታ ወደ ፊትና ወደ ቀኝ ታጥፈው እንዲጓዙ  ይፈቅዳል፡፡

ይህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክት ከግራ ወደ ቀኝ ቀጥታ፣ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ታጥፈው የሚሄዱ አሽከርካሪዎች እንዲያልፉ ይፈቅዳል፡፡



## *ሀ. የአሽከርካሪዎች የመተላለፊያ የእጅ ምልክት አሰጣጥና ጠቀሜታ*

ፍሬቻ ወይም የፍሬን መብራት በብልሽት ምክንያት በማይሠራበት ወይንም  በግልጽ ከርቀት በማይታይበት ጊዜ ተሽከርካሪዎች፡-

- ከቆሙበት ቦታ ተነስተው ጉዞ ሲቀጥሉ፣
- የያዙትን ነጠላ መሥመር ትተው ወደሌላ ሲለውጡ፣
- የሚከተሉትን ተሽከርካሪ ሲቀድሙ፣
- ወደግራ ወይም ወደቀኝ ሲታጠፉ፣
- በስተግራ ወደ ኋላ ዞረው ሲጓዙ፣
- የሚያዩትን ተሽከርካሪ እንዲያልፍ ሲፈቅዱና ለማቆም ሲፈልጉ

የሚያሳዩዋቸው የእጅ ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1/ *ወደ ግራ ለመታጠፍ የሚሰጡ የእጅ ምልክቶች*

- *መሪው በግራ በኩል የሆነ ተሽከርካሪን የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ወደ ግራ ለመታጠፍ ወይም ከቆሙበት ለመነሳት ሲፈልጉ የሚያሳዩት የእጅ ምልክት በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ሰፍሯል፡-*

ሀ/ የግራ ጉን መስታወትን በሙሉ ማውረድ፣

ለ/ በቀኝ እጅ መሪውን በሚገባ መያዝ፣

ሐ/ የግራ እጅ መዳፍህን ወደ መሬት በማመልከት ቀጥታ ወደ ጎን ከዘረጋህ በኋላ፡-

- ወደ ግራ መታጠፍህን፣
- ከቆምክበት ሥፍራ ለመንቀሳቀስ መፈለግህን ከኋላ የሚመጡት ተሸከርካሪዎች በግልጽ እንዲረዱ አድርግ፣



- መሪው በቀኝ በኩል የሆነ ተሸከርካሪን እየነዱ ወደ ግራ የሚታጠፉ አሽከርካሪዎች የሚያሳዩት የእጅ ምልክት፡-

ሀ/ መስታወቱን በሙሉ ማውረድ፣

ለ/ መሪውን በግራ እጅህ በሚገባ መያዝ፣

ሐ/ ቀኝ እጅን በመስኮቱ አውጥቶ ክንድን ከትከሻ በላይ 45 ዲግሪ ያህል አጠፍ ማድረግ፣

መ/ መዳፍን በመጠኑ ከፍ አድርገ ጣቶችን መዘርጋት፣

ሠ/ እጅን ከትከሻ ጀምሮ ከቀኝ ወደ ግራ በማዞር፣ ከኋላ የሚከተሉ አሽከርካሪዎች ከቀኝ ወደ ግራ ለመታጠፍ መፈለግህን በግልጽ እንዲረዱት ማድረግ፡፡

**ሁልጊዜም ቢሆን ራስህንና ሌሎችን ከትራፊክ አደጋ ጠብቅ**

የብስክሌት ወይም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች ወደ ግራ ለመ ታጠፍ ሲፈልጉ በስዕሉ እንደተመለከተው የግራ እጃቸውን በትከሻቸው ትክክል ወደ ጉን በመዘርጋት ለሚከተሏቸው አሽከርካሪዎች ምልክት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡



## 2/ ወደ ቀኝ ለመታጠፍ የሚሰጡ የእጅ ምልክቶች

- የተሽከርካሪው መሪ በግራ በኩል የሆነ ተሽከርካሪን እየነዱ ወደ ቀኝ የሚታጠፉ አሽከርካሪዎች የሚያሳዩት የእጅ ምልክት፡-

  ሀ/ መስተዋቱን በሙሉ ማውረድ፣

  ለ/ መሪውን በቀኝ እጅህ አጥብቆ መያዝ፣

  ሐ/ የግራ እጅህን በመስኮት በማውጣት ወደ ላይ 45 ዲግሪ ያህል አጠፍ ማድረግ፣

  መ/ መዳፍን በመጠኑ ከፍቶ ጣቶችን መዘርጋት፣

  ሠ/ ከትከሻ ጀምሮ ከግራ ወደ ቀኝ በማዞር ከኋላ ለሚከተሉ አሽከርካሪዎች ከግራ ወደቀኝ ለመታጠፍ መፈለግን በግልጽ እንዲረዱት ማድረግ፡፡



## 3/ መሪው በቀኝ ሆኖ ወደ ቀኝ ለመታጠፍ የሚሰጡ የእጅ ምልክቶች

- መሪው በቀኝ በኩል የሆነ ተሽከርካሪን የሚያሽከረክሩ ሰዎች ወደ ቀኝ ለመታጠፍ ወይም ከቆሙበት ለመነሳት ሲፈልጉ የሚያሳዩት የእጅ ምልክት ፡-

  ሀ/ የቀኝ ጐን መስታወቱን በሙሉ ማውረድ፣

  ለ/ በግራ እጅ መሪውን በሚገባ መያዝ፣

  ሐ/ የቀኝ እጅ መዳፍን ወደ መሬት በማመልከት ቀጥታ ወደ ጐን ከዘረጉ በኋላ፡-

- ⇨ ወደ ቀኝ መታጠፍንና ከቆምክበት ሥፍራ ለመንቀሳቀስ መፈለግ ህን ከኋላ የሚከተሉ ተሽከርካሪዎች በግልጽ እንዲረዱት አድርግ፡፡



. ወደቀኝ ለመታጠፍ የሚፈልግ የብስክሌት ወይም የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ መሪውን በግራ እጁ በመያዝ የቀኝ እጁን በትከሻው ትክክል ወደ ጐን ዘርግቶ ወደቀኝ ለመታጠፍ መፈለጉን ለሚከታተሉት አሽከርካሪዎች በግልጽ አሳይቶ መታጠፍ ይገባዋል፡፡



## 4.4 በመንገድ ላይ የሚሠሩ መስመሮች

- የት ቦታ ላይ ወደ ሌላ አቅጣጫ ገብተን መቅደም እንደምንችል ወይም እንደማንችል ይጠቁማሉ፤
- ለመታጠፍና ዞሮ ለመመለስ የምንጠቀምበትን ረድፍ ያመለክታሉ፤
- በትራፊክ መብራት አካባቢ የምንቆምበትን ሥፍራ ያመለክታሉ፤
- የመንገድ መሐልና ጠርዝን ያመለክታሉ፤
- ለእግረኞች መተላለፊያ የተከለሉ ሥፍራዎችን ያመለክታሉ፤
- አንድን መንገድ በሁለት ነጠላ መንገዶች ይከፈላሉ፤
- አንድ አቅጣጫ መንገድን በረድፍ ይከፋፍላሉ፤
- የመንገድ ዳር ምልክቶችን መትከል አስቸጋሪ በሆነበት መንገድ ላይ ምልክቶችን ተክተው ይሠራሉ፡፡

በመንገድ ላይ የሚሰመሩ መስመሮች በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፦

1. በመንገድ አግድመት የሚሰመሩ እና
2. በመንገድ አቅጣጫ የሚሰመሩ ናቸው፡፡

### *1/ <u>በመንገድ አግድመት የሚሰመሩ መስመሮች</u>*

በአጭር ርቀት ውስጥ እግረኞች መንገድ ማቋረጥ እንዲችሉ የሚሰመር መስመር ነው፡፡ አሽከርካሪዎች በዚህ መስመር ውስጥ በመንቀሳቀስ ላይ ላሉ እግረኞች ምን ጊዜም ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡



## *2/ በመንገድ አቅጣጫ የሚሰመሩ መስመሮች*

### *ሀ/ አንድ መንገድ በተቆራረጠ መስመር ለሁለት ሲከፈል፡-*

ሁሉም አሽከርካሪዎች የየራሳቸውን አቅጣጫ ተከትለው ያሽከረክራሉ፤ መታጠፍ፣ ዞሮ መመለስና ወደ ሌላ አቅጣጫ ገብቶ መቅደም የፈለገ አሽከርካሪ እንደ መንገዱና እንደ ትራፊኩ ሁኔታ በጥንቃቄ የተቆራረጠውን መስመር አልፎ መሄድ ይቻላል፡፡

ይህ መስመር የትራፊክ መጨናነቅ በማይበዛባቸው ወይም ለዕይታ አስቸጋሪ ባልሆኑ መንገዶች ላይ በመሰመር ለአሽከርካሪዎች ግልጽ የሆነ መልዕክት ያስተላልፋል፡፡



### *ለ/ አንድ መንገድ ባልተቆራረጠ /ድፍን/ ለሁለት ሲከፈል፡-*

ማንኛውም አሽከርካሪ ያልተቆራረጠውን መስመር አልፎ ዞሮ መመለስ፣ መቅደምና ታጥፎ መሄድ አይችልም። ነገር ግን እንደ መንገዱና እንደ ትራፊኩ ሁኔታ መሰመሮቹን ሳይረግጥ በራሱ ነጠላ መንገድ ላይ የግራ ረድፉን ይዞ መቅደም ይችላል።



*ሐ/ አንድ መንገድ በተቆራረጠ እና ባልተቆራረጠ መስመር ለሁለት ሲከፈል፦*

- *በተቆራረጠው መስመር በኩል ያለው አሽከርካሪ፡- ሁለቱንም መስመሮች አልፎ መቅደም፣ ዞሮ መመለስና ታጥፎ መሄድ ይችላል።*
- *ባልተቆራረጠው መስመር በኩል ያለ አሽከርካሪ፡-* መስመሮቹን አልፎ መቅደም ዞሮ መመለስና መታጠፍ አይፈቀድለትም። ነገር ግን እንደ መንገዱና እንደ ትራፊኩ ሁኔታ መስመሮቹን ሳይረግጥ በራሱ ነጠላ መንገድ ላይ የግራ ረድፉን ይዞ መቅደም ይቻላል።



*መ. አንድ መንገድ ከመስመር በተሰራ የትራፊክ ደሴት ለሁለት ሲከፈል፦*

ማንኛውም አሽከርካሪ የትራፊክ ደሴትን ረግጦ መቅደም፣ ዞሮ መመለስና መታጠፍ አይፈቀድለትም። ዞሮ መመለስና መታጠፍ የፈለገ አሽከርካሪ እንደመንገዱና እንደ ትራፊኩ

ሁኔታ በጥንቃቄ በደሴቱ መቋረጫ ለመታጠፍና ለመዞር በተዘጋጀው ሥፍራ ላይ ወደ ቀኝ አስፍቶ ዞሮ መመለስና መታጠፍ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ቀድሞ በተገለጸው ሁኔታ ደሴቱን ሳይረግጥ በራሱ ነጠላ መንገድ የግራ ረድፉን ይዞ መቅደም ይችላል፡፡



***ሠ/ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ በተቆራረጠ ነጭ መስመር በረድፍ ሲከፋፈል፡-***

ማንኛውም አሽከርካሪ በራሱ ረድፍ ውስጥ በማሽከርከር ፍጥነት ለመጨመር፣ ለመቀነስ ወይም ለመታጠፍ በሚፈለግበት ወቅት የተቆራረጠውን መስመር አልፎ ማሽከርከር ይችላል፡፡ መንገዱ ባለ አንድ አቅጣጫ በመሆኑ ዞሮ መመለስ ክልክል ነው፡፡



***ረ/ በመገናኛ /አደባባይ/ መንገዶች መድረሻ ላይ የሚሰመር መስመርና አቅጣጫ አመልካች ቀስት፡-***

- ማንኛውም አሽከርካሪ የተቆራረጠውን መስመር ጨርሶ ድፍን መስ መር ውስጥ ከመግባቱ በፊት ወይም ከመገናኛው መንገድ በ50 ሜትር ርቀት በመንገድ ላይ ባለው የቀስት ምልክት መሠረት የሚሄድበትን አቅጣጫ በመምረጥ መቅደም ይችላል፡፡
- የተቆራረጠውን መስመር ጨርሶ ድፍን መስመር ውስጥ ከገባ በኋላ ከመገናኛው መንገድ በ30 ሜትር ክልል ውስጥ አቅጣጫ እንዲቀይርና እንዲቀድም አይፈቀድለትም፡፡



## 4.5 በመንገድ ላይ የሚቀቡ ቅቦች

በመንገድ ላይ የሚቀቡ ቅቦች በሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፡-

- ***የመቆሚያ ሥፍራ ቅብ፦*** አሽከርካሪዎች በምልክቱ ውስጥ ለማቆሚያ በተዘጋጀው ሥፍራ ላይ ብቻ መቆም አለባቸው፡፡
- ***የማስተላለፊያ ምልክት ቅብ፦*** የቀለም ነጠብጣብ ባላቸው ክልሎች ውስጥ ማሽከርከር ክልክል ነው፡፡
- ***ቅድሚያ ስጥ የሚል ምልክት ቅብ፦*** ምልክቱ /ቅቡ/ ቅድሚያ ለተላላፊ በመስጠት በጥንቃቄ ማሽከርከር እንዳለብህ መልእክት ያስተላልፋል፡፡



በአራት አቅጣጫም ሆነ በማንኛውም መገናኛ መንገድ ላይ መንገዶች ከሚገናኙበት ማዕዘን ወይም ኩርባ ከ12 ሜትር ባነሰ ርቀት ውስጥ አቁሞ መሔድ ክልክል ነው፡፡



በመንገዱ ቀኝና ዳርቻ መኪናን ለማቆሚያ አመቺ በሚሆን ዓይነት በመንገድ ባለሥልጣን ለአንድ መኪና ስፋቱም ሆነ ቁመቱ ይበቃል ተብሎ በተቀባ ክልል ውስጥ አለአግባብ አቁሞ መሔድ ክልክል ነው፡፡



በቤንዚን ማደያ አካባቢዎች ተሽከርካሪዎች ወደ ማደያው ገብተው ለመቅዳት በሚያዳግታቸው ሁኔታ ከ12 ሜትር ባነሰ ውስጥ አቁሞ መሔድ ክልክል ነው፡፡



የመንገዱን የቀኝ ጠርዝ አስጠግተው በአግባቡ በቆሙ ተሽከርካሪዎች ጎን በተደራቢነት ማቆም ክልክል ነው፡፡



በመገናኛ መንገድ አካባቢ፣ አቅጣጫን ለመለየት የቀስት ምልክት በተቀባበት መስመር ላይ፣ በቅድሚያ መስመራቸውን ለይተው ለሚሔዱ አሽከርካሪዎች ያልተቆራረጠውን የመስመር ክልል የግድ እንዲያቋርጡ በሚያስገድዳቸው ርቀት ውስጥ አቁሞ መሔድ የተከለከለ ነው፡፡



መገናኛ መንገድ ውስጥ ከመደረሱ በፊት እንደ ትራፊክ ደሴት እንዲያገለግሉ በሰፊው በተቀቡ የቀለም ቅቦች ላይ ሌሎች አሽከርካሪዎች የግድ እንዲረግጧቸው ከሚያደርግ ጠባብ መንገድ ላይ ማቆም የተከለከለ ነው።





በባለ አንድም ሆነ በባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ ላይ እየነዳህ ቆይተህ መኪናህን በአካባቢው ለብዙ ጊዜም ሆነ ለተወሰነ ጊዜ የምታቆም ከሆነ ከመንገዱ ወጣ ብሎ በስተቀኝ በኩል ለማቆም በተዘጋጀው ሥፍራ ላይ ማቆም ግዴታህ መሆኑን አትዘንጋ።



ለእግረኞች ማቋረጫ የቀለም ምልክት በተሰመረበት ክልል ውስጥ ማቆም ክልክል ነው።



ከአጥር ክልል ወይም ከግቢ ውስጥ ሌሎች ተሽከርካሪዎች እንዲወጡበት በተሰራ መንገድ ላይ መተላለፊያውን ዘግቶ ማቆም ክልክል ነው።

## በመታጠፊያ መንገዶች ላይ ተተክለው ስለሚገኙ ልዩ ልዩ አንፀባራቂ ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች በመታጠፊያ ወይም አደገኛ ኩርባዎች እና መንገዱ ፊት ለፊት በማይቀጥልበት መገናኛ ስፍራ ላይ አሽከርካሪዎች የመንገዱን ክልል አልፈው እንዳይወጡ የሚያስጠነቅቁ ምልክቶች ናቸው።

ምልክቶቹ ጥቁርና ነጭ ቀለም በተቀቡ ትክል ድንጋዮች የመታጠፊያ፣ የገደላማ ወይም የድልድይ አካባቢ ተጀምሮ እስከሚያልቅበት ቦታ ድረስ ተተክለው የሚታዩ ሲሆን፣ በተጨማሪም መንገዱ

ፊት ለፊት በማይቀጥልበትና አደገኛ መታጠፊያ ስፍራዎች ላይ አግድም የተተከሉ ሰሌዳዎች በአንፀባራቂ ነጭና ጥቁር ቀስት የመንገዱን አቅጣጫ ያመለክታሉ፡፡
ከላይ የተገለፁ ምልክቶችን በተመለከተ ከዚህ ቀጥሎ ከሚቀርቡት መጠነኛ ስዕላዊ ማብራሪያዎች መረዳት ይቻላል፡፡

1. ወደ ግራ የሚታጠፍ አደገኛ ኩርባ መንገድ ላይ የሚተከል የማስጠንቀቂያ ምልክት፡፡



2. ፊት ለፊት የሚቀጥል መንገድ ያለመኖሩን የሚያስጠነቅቅ የቀስቱንና የትክል ድንጋይ አንፀባራቂ ምልክት፡፡



2. ወደ ቀኝ የሚታጠፍ አደገኛ መጠምዘዣ መንገድ ላይ የሚተከል የማስጠንቀቂያ አንፀባራቂ ምልክት፡፡



z